# የ ስ ደ ት ፡ መ ታ ሰ ቢ ያ ።

ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረ ፡ ዘመን ፤

ወ ደ ፡ ኢ የ ሩ ሳ ሌ ም ፡ ስ ደ ት ።


ተ ጻ ፈ ፤

ከተአምራት ፡ ይገዙ ፤

ኢትዮጵያዊ ፡ ስደተኛ ፡


ተጎትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፳ ፡ ወ፫ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡

ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።


አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ. ም.

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።



www.ethiopianorthodox.org

14/4-53

# የ ስ ደ ት ፡ መ ታ ሰ ቢ ያ ።

ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረ ፡ ዘመን ፤
ወ ደ ፡ ኢ የ ሩ ሳ ሌ ም ፡ ስ ደ ት ።

ተ ጻ ፈ ፤


ከተአምራት ፡ ይገዙ ፤
ኢትዮጵያዊ ፡ ስደተኛ ፡



ተንትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፳ ፡ ወ፪ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡
ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ. ም.
በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።



www.ethiopianorthodox.org

ያህል ፡ በምሥር ፡ የኖሩ ፡ የመንግ ፡ ሰው ፡ «አራሚስ ፡» ውስጥ ፡ መጥተው ፡ ተቀበሉን ። ስንገናኛቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንባቸውን ፡ ያዙሩ ፡ ነበር ። ከእሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ልጅ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሚካኤል ፡ ማህሉ ፡ የተባለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የተወለደ ፡ በአባቱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በእናቱ ፡ ምሥር ፡ ነበር ። የዕድሜው ፡ ልጅነት ፡ እኩያዬ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ መጀመሪያ ፡ እኔን ፡ መጥቶ ፡ ከጀርባዬ ፡ ነክቶ ፡ «ስማ ፡ እኔ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነኝ ፡» ብሎ ፡ ሳመኝ ። ተሸክሜ ፡ የነበረውን ፡ መነጽር ፡ ተቀብሎ ፡ ያዘው ፡ ወዲያው ፡ ከሌሎቹም ፡ ጋራ ፡ ተዋወቀ ። የምንጋገረው ፡ ጓደኛ ፡ በማግኘቴ ፡ ልቤ ፡ የደስታ ፡ ድጋፍ ፡ አገኘ ።

ከመርከቡ ፡ ወርደን ፡ ዕቃችንን ፡ በኩሊ ፡ አሲዘን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቆንስላ ፡ ገባን ። ቆንስሉ ፡ አቶ ፡ ይልማ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ በዚያን ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄደው ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ አላገኘናቸውም ፡

ፖርት ፡ ሳይድ ፡ በጥርብ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠሩ ፡ ብዙ ፡ የተዋቡ ፡ ፎቆች ፡ ቤቶች ፡ ያሉበት ፡ ከተማ ፡ ናት ። አቀማመጧም ፡ በሜዴቴራኒ ፡ ባሕርና ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ መገናኛ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ወደሩቁ ፡ ምሥራቅ ፡ ለመሄድ ፡ የቀረበው ፡ መተላለፊያ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በወደቧ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ መርከቦች ፡ ቁመው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።

በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ከአገሩ ፡ ተወላጅ ፡ ይልቅ ፡ የኢጣልያና ፡ የግሪክ ፡ ተወላጅ ፡ ይበዛል ። ሌሎችም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ይታዩበታል ። «ካናል ፡ ዱ. ሱዌዝ» የተባለውን ፡ ሰፊ ፡ ቦይ ፡ ቀዶ ፡ ቀይ ፡ ባሕርን ፡ ከሜዲቴራኒ ፡ ጋራ ፡ የቀላቀለ ፡ ፌርዲናን ፡ ደሌሴፕስም ፡ «በሩ ፡ ይኸው» ብሎ ፡ የሚያሳይ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ በሐውልቱ ፡ ይታያል ። ፖርት ፡ ሳይድ ፡ ምንም ፡ በረሃ ፡ ቀመስ ፡ ከተማ ፡ ብትሆን ፡ በዐባይ ፡ ወንዝና ፡ በካናል ፡ ዱ. ሱዌዝ ፡ ውሃ ፡ የተከበበች ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ሙቀቱ ፡ እጅግ ፡ የሚሰማ ፡ አልነበረም ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመግባት ፡ የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ እስቲፈቅድልን ፡ ድረስ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቆንስላ ፡ ቈየን ። ቆንስላው ፡ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ በመነከርና ፡ (ዋና ፡ አላውቅም ፡ ነበር) በፌርዲናን ፡ ዳሌሴፕስ ፡ ሐውልት ፡ ዙሪያ ፡ በመዘዋወር ፡ ከተማዪቱ ፡ አልሰለቸችንም ፡ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ልዩ ፡ ፍሬዎች ፡ ከግንቦት ፡ እስከ ፡ ሐምሌ ፡ ወር ፡ የሚያፈራ ፡ በመልክ ፡ እንኰይ ፡ መስሎ ፡ ትንሽ ፡ ከእንኰይ ፡ የሚበልጥ ፡ ድቡልቡል ፡ ቀይ ፡ ፍሬ ፡ ነው ።

ጣዕሙም ፡ አገራችን ፡ ካሉ ፡ ፍሬዎች ፡ ጋራ ፡ ሳወዳድረው ፡ ያልተቻለኝ ፡ እጅግ ፡ ጣፋጭ ፡ ፍሬ ፡ ነው ። ከላይ ፡ እንዳልሁት ፡ ሚሽሚሻችንን ፡ እየበላን ፡ ስንጓዝ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ልክ ፡ ፰ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ደረስን ። እዚያም ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌን ፡ መምጣታችንን ፡ በቴሌግራም ፡ አስታውቀናቸው ፡ ነበርና ፡ አገኘናቸው ። ከእርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ አቶ ፡ ኪዳኔ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ የተባለው ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቆንስላ ፡ አጋፋሪ ፡ ሊቀበለን ፡ መጥቶ ፡ ነበር ። የኢየሩሳሌም ፡ የባቡር ፡ ማረፊያ ፡ ጣርያቸው ፡ ቆርቆሮ ፡ ሁኖ ፡ በግንብ ፡ የተሠሩ ፡ ትንንሽ ፡ የምድር ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። አሠራራቸውና ፡ የጽዳታቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በቀድሞው ፡ አሮጌው ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ይመስላል ፡ እላለሁ ።

ፓስፖራችንን ፡ ለይለፍ ፡ ሹም ፡ ካሳየን ፡ በኋላ ፡ ዕቃችንን ፡ በአውቶሞቢል ፡ አሳፍረን ፡ ከጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌና ፡ ከአቶ ፡ ኪዳኔ ፡ ጋራ ፡ ሁነን ፡ ደብረ ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ደረስን ። እዚያም ፡ እንደ ፡ ደረስን ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነንም ፡ ለጸሎት ፡ መጥተው ፡ አገኘናቸው ። ደጃዝማች ፡ ይገዙም ፡ በደብረ ፡ ገነት ፡ የእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ገብተው ፡ ከግርማዊትነታቸው ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኀዘን ፡ ተወያይተው ፡ ተለያዩ ። ከዚያ ፡ ብዙ ፡ እጨጌንና ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ሥላሴን ፤ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰውን ፤ ቀኛዝማች ፡ ሙሉ ፡ ጌታን ፡ አግኝተን ፡ ተገናኝተን ፡ እኡንም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኀዘን ፡ ተወያዩ ።

ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ተከራይተው ፡ እንዲቈዩን ፡ የነበረው ፡ ቤት ፡ የውሉ ፡ ጉዳይ ፡ ሳይፈጸም ፡ ቈይቶን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እዚያው ፡ እደብረ ፡ ገነት ፡ አባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ የተባሉ ፡ መነኵሴ ፡ አንድ ፡ ያማረች ፡ እልፍኝ ፡ ሰጥተውን ፡ ዕቃችንን ፡ አሳርፈን ፡ መኝታችንንም ፡ አሰናዳን ። ብዙ ፡ እጨጌና ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ሥላሴ ፤ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፤ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፤ ቀኛዝማች ፡ ሙሉ ፡ ጌታም ፡ እዚያው ፡ ገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ ወይዘሮ ፡ አልታየ ፡ ወርቅ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነቴ ፡ ወደ ፡ ጀኔብ ፡ የመጣሁበት ፡ ምክንያት ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቴ ፡ ዋና ፡ መሪ ፡ ሆኜ ፡ ራሴ ፡ ከተዋጋሁ ፡ በኋላ ፤ ከብዙ ፡ ሺ ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ የቈየውን ፡ ነጻነቱን ፡ ለመጠባበቅ ፡ ስለሚታገለው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለመከላከልና ፡ ይህንም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የተገባኝን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ነው። እነዚህም ፡ የተከተሉኝ ፡ ሹማምቶች ፤ ራሳቸው ፡ ከደረሰባቸውና ፡ ምስክር ፡ ከሆኑት ፡ ከሚያስቅቅ ፡ ነገር ፤ በሕዝቤም ፡ ላይ ፡ ከተደረገው ፡ ሥቃይ ፡ የዓለምን ፡ መንግሥታት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲጠብቃቸው ፡ እለምናለሁ ።

በጀኔብ ፡ የተሰበሰቡትና ፡ ለብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ሰዎች ፡ ሴቶችና ፡ ሕፃናት ፡ ሕይወት ፡ አላፊ ፡ ለሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ እንደራሴዎች ፡ በነዚህ ፡ ፍጥረቶች ፡ የደረሰባቸውን ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የደረሰባትን ፡ ዕድል ፡ በዝርዝር ፡ አስረዳለሁ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጦርነት ፡ ያደረገው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ይልቁንም ፡ ከጦርነቱ ፡ ስፍራ ፡ በራቁት ፡ በሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በድንጋጤ ፡ ለመግደልና ፡ ዘራቸውንም ፡ ለማጥፋት ፡ አደጋ ፡ እየጣለ ፡ ወጋቸው ።

ጦርነቱ ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም. የኢጣሊያ ፡ አውሮፕላኖች ፡ በጦር ፡ ሠራዊቶቼ ፡ ላይ ፡ ጋዝ ፡ ላክሪሞዤን ፡ ያለበት ፡ ቦምብ ፡ ጣሉባቸው ። ይህም ፡ ቦምብ ፡ እጅግ ፡ አልጐዳቸውም ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ወታደሮቼ ፡ ቦምብ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ ጋዙን ፡ ነፋስ ፡ እስኪወስደው ፡ ድረስ ፡ መበታተኑን ፡ ስላወቁበት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኢጣሊያ ፡ አውሮፕላኖች ፡ ኤፔሪት ፡ የተባለውን ፡ ጋዝ ፡ መጣል ፡ ጀመሩ ። በኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ ኤፔሪት ፡ ያለበት ፡ በርሜል ፡ ወደቀባቸው ። ይኸውም ፡ ሆኖ ፡ የኤፔሪቱ ፡ ጋዝ ፡ ያደረገው ፡ ጉዳት ፡ የለም ። ምክንያቱም ፡ የኤፔሪት ፡ ውሃ ፡ የሚያገኛቸው ፡ ወታደሮች ፡ ጥቂቶች ፡ ስለ ፡ ነበሩና ፡ በርሜሉ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ወታደሮቹም ፡ ሕዝቡም ፡ መርዝ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ስላወቁት ፡ ነው ።

የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ጠቅላይ ፡ ሹም ፡ መቀሌን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ በከበቡ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መፈታቱን ፡ ስለ ፡ ተረዳውና ፡ ስለ ፡ ሠጋ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ የኤፔሪት ፡ አጣጣል ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

አደረገ ። ይህንም ፡ አደራረግ ፡ አሁን ፡ ለዓለም ፡ ገልጦ ፡ ማስታወቅ ፡ የተገባኝ ፡ ነው ።

በአይሮፕላኖቹ ፡ ላይ ፡ የኤፔሪቱን ፡ ውሃ ፡ የሚረጭ ፡ መኪና ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ሰፊ ፡ በሆነው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሞትን ፡ የሚያመጣ ፡ ረቂቅ ፡ ዝናብ ፡ እንዲወርድበት ፡ ተደረገ ፡ የኢጣሊያም ፡ አውሮፕላኖች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ፡ እየሆኑና ፡ እየተመላለሱ ፡ የኤፔሪት ፡ ዝናብ ፡ ሳያቋርጥ ፡ እንዲወርድ ፡ አደረጉ ። በጥር ፡ መጨረሻ ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ በወታደሮቻችን ፤ በሴቶችና ፡ በልጆች ፤ በከብቶችና ፡ በፈሳሽ ፡ ወንዞች ፤ በኩሬዎችና ፡ በከብት ፡ መሠማሪያዎች ፡ በታዎች ፡ ላይ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ሞት ፡ የሚያመጣ ፡ ይህ ፡ ዝናብ ፡ ዘነበባቸው ፡ ፍጡር ፡ የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ በፍጹም ፡ ለማጥፋት ፡ ውሃውንና ፡ ለከብት ፡ የሚሆነውንም ፡ ሣር ፡ መርዝ ፡ ብቻ ፡ ለማድረግ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ አይሮፕላኖቹ ፡ ይህንኑ ፡ ሥራቸውን ፡ እየተመላለሱ ፡ እንዲሠሩ ፡ አደረገ ። ዋና ፡ የጦርነት ፡ መሣሪያ ፡ ያደረገው ፡ ይህንኑ ፡ ነው ።

ይኸም ፡ በረቂቅነት ፡ የሚሠራ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ጦርነቱ ፡ ከሚደረግበት ፡ ቦታ ፡ በራቁት ፡ ቦታዎች ፡ የሚገኙትን ፡ ሕዝብ ፡ አጠፋቸው ። አገራቸውንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አደረገው ፤ አሳቡም ፡ በሚበዛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ድንጋጤንና ፡ ሞትን ፡ ለመዝራት ፡ ነበር ።

እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ የሚያመጣ ፡ ይህ ፡ ብልሃት ፡ ተፈጸመበት ፤ ሰውም ፡ ከብትም ፡ በፍጹም ፡ አለቀ ። ከአውሮፕላንም ፡ የሚወርደው ፡ የሞት ፡ ዝናም ፡ የሚነካውን ፡ ሁሉ ፡ እያሠቀየ ፡ ያበርር ፡ ነበር ። ይህም ፡ የመርዝ ፡ ዝናብ ፡ የዘነበበትን ፡ ውሃ ፡ የሚጠጡ ፤ መርዙም ፡ የሚነካውን ፡ ምግብ ፡ የሚመገቡ ፡ በታላቅ ፡ ሥቃይ ፡ አለቁ ። በኢጣሊያ ፡ ኤፔሪት ፡ ምክንያት ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚገመቱ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ። እኔም ፡ ወደ ፡ ጄኔብ ፡ ለመምጣት ፡ የቈረጥሁት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የደረሰበትን ፡ ሥቃይ ፡ ለሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ለማስታወቅ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ የማያከራክር ፡ ምስክርነት ፡ እኔና ፡ ከነዚህ ፡ ከተከተሉኝ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ የተሻለ ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ የሚያስረዳ ፡ አይገኝም ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ በኦሬሲዩል ፡ በተነገረው ፡ የዲስኩር ፡ ቃል ፡ እንደ ሚታየው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ለጠብ ፡ ማሰቡ ፡ ምንም ፡ የሚያ ጠራጥር ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በየጊዜያቱ ፡ አስታወሰ ።

ጠቡ ፡ ከተነሣ ፡ ጀምሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ነገሩን ፡ በሰላም ፡ ለመጨረስ ፡ ፈለገ ። በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በተጻፈው ፡ ቃል ፡ ነገሩ ፡ እንዲታይ ፡ ጠየቀ ። የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም. በኢትዮጵያና ፡ በኢጣሊያ ፡ መከከል ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ነገሩ ፡ እንዲታይ ፡ ስለ ፡ ፈቀደ ፡ የኢትዮጵያም ፡ መንግሥት ፡ ይህንኑ ፡ ተቀበለ ። የሽምግልና ፡ ዳኞችም ፡ ነገሩን ፡ በመልከም ፡ ሳይፈርዱለት ፡ ቢቀሩ ፡ እንኳ ፡ ፍርዱን ፡ በመልከም ፡ ፈቃድ ፡ እፈጽማለሁ ፡ ብሎ ፡ አስታወቀ ። የሽምግልና ፡ ዳኞቹም ፡ ወልወል ፡ የማን ፡ ግዛት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገሩን ፡ እንዲያዩ ፡ ኢጣሊያ ፡ ሳትፈቅድ ፡ ስለ ፡ ቀረች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይህንም ፡ ተቀበለች ። ይህንም ፡ ነገር ፡ የሚመረምሩ ፡ ነጻ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በአገሩ ፡ እንዲላኩ ፡ የምክሩ ፡ ጉባኤ ፡ ጠየቀ ። የምክሩ ፡ ጉባኤ ፡ በፈቀደው ፡ ዐይነት ፡ የቈረጠውን ፡ ምርመራ ፡ ለመቀበል ፡ የተዘጋጀ ፡ መሆኑን ፡ አስታወቀ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በበኩሉ ፡ የወልወል ፡ ነገር ፡ በሽማግሎች ፡ ታይቶ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ የፈቀደውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እንዲችል ፡ ነጻነቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ የማመልከቻውን ፡ ዝርዝር ፡ ለምክሩ ፡ ጉባኤ ፡ አቀረበ ። ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመጨረስ ፡ በማኅበሩ ፡ ውል ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ለማስፈጸም ፡ ብቻ ፡ የሚበጅ ፡ ነገር ፡ የለበትም ፡ ብሎ ፡ አስረገጠ ። ደግሞ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ዋና ፡ የሕይወቱ ፡ ጥቅም ፡ ያለበት ፡ ስለ ፡ ሆነና ፡ ራሱን ፡ ለመጠበቅ ፡ ዋና ፡ መጀመሪያ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ተስፋውን ፡ በጭራሽ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ካላነሣና ፡ የራሱን ፡ ጥቅምና ፡ ቅኝ ፡ አገሩንም ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ሙሉ ፡ ነጻነቱን ፡ ካላገኘ ፡ በተቀር ፡ ኢጣሊያ ፡ ከሁሉ ፡ ያነሰ ፡ መጀመሪያ ፡ ማድረግ ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ማገደል ፡ ይሆንበታል ፡ ብሎ ፡ አደላድሎ ፡ አስታወቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

መንግሥቶችም ፡ እኔን ፡ ለመከልከል ፡ ሲሉ ፡ መሣሪያ ፡ ከአገር ፡ እንዳይወጣ ፡ ከለከሉ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ በካናል ፡ ስዊስ ፡ በኩል ፡ መሣሪያና ፡ ጥይት ፤ ወታደርም ፡ ሳያቋርጥና ፡ ማንም ፡ ሳይከለክለው ፡ ለማስተላለፍ ፡ ችሎ ፡ ነበር ። በመስከረም ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደር ፡ ግዛቴን ፡ አገሬን ፡ ወረረው ። ከጥቂት ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ብቻ ፡ ወታደር ፡ እንዲሰበሰብ ፡ የክተት ፡ አዋጅ ፡ አደረግሁ ። ሰላምን ፡ ጠብቆ ፡ ለመኖር ፡ በመፈለግ ፡ አሳብ ፤ በታላቁ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ጦርነቱ ፡ ሊደርስ ፡ አቅራቢያ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ አደረገው ፡ ሁሉ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ጠብ ፡ ፈላጊነት ፡ እንዳይነሣ ፡ በማለት ፡ ወታደሮቼ ፡ ሠላሳ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለሱ ፡ አደረግሁ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱ ፡ ለምክሩ ፡ ጉባኤ ፡ እንዳመለከትሁት ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ ግፍ ፡ ይቀጥል ፡ ጀመር ።

በዚህ ፡ በማይወዳደር ፡ ጦርነት ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ የሚገዛ ፡ የሚያስፈልገውንም ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ የሚችል ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ለማጥፋት ፡ በያይነቱ ፡ የሆነ ፡ መሣሪያ ፡ ለመሥራት ፡ የቴክኒክ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ያለው ፡ መንግሥት ፡ ያለ መሣሪያ ፤ ያለገንዘብ ፡ ትክክል ፡ ፍርድንና ፡ የነገሥታትን ፡ ማኅበር ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ተማምኖ ፡ ከተቀመጠው ፡ ትንሽ ፡ ከሆነ ፡ ከ፲፪ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በተደረገው ፡ በዚህ ፡ በማይወዳደር ፡ ጦርነት ፤ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ የማኅበሩን ፡ ውል ፡ አፍርሷል ፡ ተብሎ ፡ ከተፈረደና ፡ አጥቂውም ፡ እንዳያሸንፍ ፡ እንከለክላለን ፡ ከተባለ ፡ በኋላ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የተደረገው ፡ ያገኘውም ፡ ርዳታ ፡ እንደሌለ ፡ እናንተ ፡ ልትገምቱት ፡ ትችላላችሁ ። በማኅበሩ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ አንዱ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ በማኅበሩ ፡ ውል ፡ በ፲፮ኛው ፡ ክፍል ፡ ተጽፎ ፡ የፈረመው ፡ ፊርማ ፡ እንደሚያዘው ፡ ሁሉ ፡ አጥቂው ፡ ያደረገው ፡ ጦርነት ፡ በያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ላይ ፡ በራሱ ፡ እንደተደረገበት ፡ ሁሉ ፡ ቈጥሮት ፡ የለምን ?

ይህ ፡ ውል ፡ የተገባበት ፡ ቃል ፡ ይፈጸማል ፡ ብዬ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋዬን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አድርጌ ፡ ነበር ። ተስፋዬም ፡ ደግሞ ፡ አጥ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ያቈዩታል ። በጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም. የተደረገው ፡ የም
ስጢር ፡ ውል ፡ ይህን ፡ የማሰናከል ፡ ሥራ ፡ አስቀድሞ ፡ ያመለክት ፡
ኖሩዋልን ?

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በቀጥታ ፡ ጥቅማቸው ፡ ያልተነካባ
ቸው ፡ ሌሎች ፡ መንግሥቶች ፡ የመንግሥታትን ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡
ለመከላከል ፡ የወታደሮቻቸውን ፡ ደም ፡ ያፍሱ ፡ ብሎ ፡ አልጠበቀም ።
የኢትዮጵያ ፡ ጦረኞች ፡ ጠይቀው ፡ የነበሩት ፡ ለመከላከያ ፡ የሚሆና
ቸውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መሣሪያ ፡
ለመግዣ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ጠይቌ ፡ ነበር ። ይህንም ፡
ርዳታ ፡ ተከለከልሁ ። በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ባ፲፮ኛው ፡
ክፍል ፡ የተጻፈው ፡ ቃልና ፡ መንግሥቶች ፡ እየተባበሩ ፡ በመረዳዳት ፡
ጸጥታ ፡ እንዳይጠፋ ፡ ያደርጋሉ ፡ የተባለው ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ትርጓሜ ፡
ምን ፡ ይሆን ?

ከጅቡቲ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ያለው ፡ የምድር ፡ ባቡር ፡
ለኢትዮጵያ ፡ የሚሆን ፡ መሣሪያ ፡ እንዲተላለፍበትና ፡ ለኢትዮጵያ ፡
መንግሥት ፡ እንዲያገለግል ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ መሣሪያው ፡ በዚያ ፡
በኩል ፡ እንዳይገባ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ተደረገ ። ላሁኑ ፡ ሰዓት ፡
ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያላገባብ ፡ ለገባው ፡ ለኢጣሊያ ፡
ሠራዊት ፤ ዋና ፡ የሥንቅና ፡ የመሣሪያ ፡ ማመላለሻ ፡ ሁኑዋል ። የነ
ትራሊቴ ፡ ደንብ ፡ እንኳ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ እስካሉበት ፡
ድረስ ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ነገር ፡ እንዳይሜን ፡ ይከለክላል ። ይህ ፡
ከሆነ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ባ፲፮ኛው ፡ ክፍል ፡ በተጻ
ፈው ፡ ቃል ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሆኑ ፡ መንግሥቶች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡
ሌላውን ፡ በአጥቂነት ፡ የወጋው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌሎቹ ፡ ኑትር ፡ መሆ
ናቸው ፡ ቀርቶ ፡ መርዳት ፡ የሚገባቸው ፡ ለአጥቂው ፡ ሳይሆን ፡ ለተ
ጠቂው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የነትራሊቴ ፡ ደንብ ፡ እዚህ ፡ መነሣት ፡ አይገባ
ውም ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ከዚህ ፡
ቀድሞ ፡ ተጠብቋልን ? ዛሬም ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡
ይቻላልን ?

አሁን ፡ በመጨረሻው ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ታላቅ ፡ አገ
ብብ ፡ ያላቸው ፡ ታላላቅ ፡ መንግሥቶች ፡ በምክር ፡ ቤታቸው ፡ አጥ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ቂው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሬት ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ከያዘ ፡ በገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ረገድ ፡ ይህ ፡ እንዳይሆን ፡ ያቆምነውን ፡ መከላከያ ፡ መቀጠል ፡ አያስፈልግም ፡ ብለው ፡ አስታወቁ ።

በአርጀንቲን ፡ መንግሥት ፡ ጥያቄ ፡ በአጥቂው ፡ በኢጣሊያ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ለመመርመር ፡ የተሰበሰበው ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ ዛሬ ፡ በፊቱ ፡ የሚገኘው ፡ አኳኋን ፡ ይህ ፡ ሆን ።

ዛሬ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ በፊቱ ፡ ያለው ፡ ጕዳይ ፡ ኢጣሊያ ፡ በአጥቂነት ፡ የሠራችውን ፡ ለመጨረስ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ በሙሉ ፡ የዓለምን ፡ መንግሥታት ፡ የሚነካ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጬ ፡ አስታውቃለሁ ። ይህም ፡ ጕዳይ ፡ ለዓለም ፡ ጸጥታ ፡ እንዲሆን ፡ መንግሥታት ፡ ለመረዳዳት ፡ የሚገባቸው ፡ ሴኩሪቴ ፡ ኰሌክቲቭ ፡ የተባለው ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ሕይወት ፤ የዓለም ፡ መንግሥታቶች ፡ ለተዋዋሉት ፡ ውል ፡ መስጠት ፡ የሚገባቸው ፡ እምነት ፡ ትንንሾቹም ፡ መንግሥቶች ፡ አገራቸውና ፡ ነጻነታቸው ፡ እንዳይነካ ፡ የተቀበሉት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የሚከበርበትና ፡ ዋጋው ፡ የሚገመትበት ፡ የመንግሥቶች ፡ ትክክልነት ፡ የተመሠረተበት ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ ለማጽናት ፡ ወይም ፡ ትንንሾች ፡ መንግሥቶች ፡ የኀይለኞች ፡ መንግሥቶች ፡ ተገዢ ፡ ለመሆን ፡ መቀበል ፡ ይገባቸው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ለመፍረድ ፡ ነው ። በአጭር ፡ ቃል ፡ የተነካውና ፡ የተበደለው ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ የተገባ ፡ አንዋወር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ አይደለችም ። በአንድ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የተፈረሙ ፡ ፊርማዎች ፤ ዋጋቸውን ፡ የሚያገኙት ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ የግል ፡ ጥቅሙን ፡ በቀጥታና ፡ በፍጥነት ፡ ለማግኘት ፡ ለመፈጸምም ፡ እንዲችል ፡ እንዲረዱት ፡ ሲሆኑ ፡ ነውን ?

በረቂቅ ፡ መንገድ ፡ መበላለጥ ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ ሊለውጠው ፡ ወይም ፡ የክርክሩን ፡ መንገድ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ሊመራው ፡ አይገባም ። ይህንንም ፡ ማመልከቻ ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ የማቀርበው ፡ በእውነተኛነት ፡ ከልቤ ፡ ነው ።

ከእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በተቀር ፡ የፍጡር ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ የሚያበላልጥ ፡ ሥራ ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነው ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ በደል ፡ የሌ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ዶለምን ? የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ለመሆን ፡ ሥልጣን ፡ ባላችሁ ፡ በታላላቅ ፡ መንግሥቶች ፡ ርዳታ ፡ የሚገኘው ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበርና ፡ ማኅበረተኞች ፡ በሚገባ ፡ ተስፋ ፡ አድርገው ፡ የሚጠብቁት ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ፍጻሜ ፡ ነውን ?

ኢጣሊያ ፡ በአጥቂነት ፡ በሠራችው ፡ ሥራ ፡ ነገሩ ፡ እዚህ ፡ ቢደርስ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሆኑት ፡ መንግሥቶች ፡ የኀይለኛውን ፡ ፈቃድ ፡ በመፈጸም ፡ ምሳሌ ፡ ለመተው ፡ ፈቃዳቸው ፡ ይሆናልን ?

የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እንዲሻሻልና ፡ የመንግሥታት ፡ መረዳዳት ፡ የሚሰጠው ፡ መተማመኛ ፡ የተፈተነ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ተብሎ ፡ በእርግጥ ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ አሳብ ፡ መቅረቡ ፡ ነው ። መለወጥ ፡ የሚገባው ፡ ውሉን ፡ ኖሮዋልን ? ውሉን ፡ የፈረሙት ፡ በውሉ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ለመጠበቅ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ካልሆነ ፡ ውሉ ፡ ቢለወጥስ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ምን ፡ መተማመኛ ፡ ይገኛል ? የጐደለው ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ አይደለም ።

የመንግሥታት ፡ ማኅበረተኛ ፡ በሆነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እንዲከበር ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ እንዲፈጸም ፡ ጉባኤውን ፡ እጠይቃለሁ ። በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከውል ፡ የተላለፈ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተደረገበት ፡ በዚሁ ፡ በተደረገበት ፡ ግፍ ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ያቀረብሁትን ፡ መቃወም ፡ አሁንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እቃወማለሁ ። በዓለም ፡ ፊት ፡ ሆኜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ በኀይል ፡ የተደረገባቸውን ፡ ነገር ፡ አይቀበሉም ። ሥርዐት ፡ እንዲያሸንፍ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እንዲከበር ፤ የሚገባቸውም ፡ ሥልጣንና ፡ ግዛት ፡ እንዲመለስላቸው ፡ የሚቻላቸውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማድረጋቸውን ፡ እገልጣለሁ ።

በተጠቃችሁ ፡ ጊዜ ፡ አጥቂው ፡ እንዳያሸንፋችሁ ፡ እንረዳችኋለን ፡ ብለው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የገቡት ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ መንግሥቶች ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ አጽንተው ፡ እንዲረዱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

የሁለተኛው ፡ የመንግሥታት ፣ የግፍ ፡ ፍርድ ፡ ያዘነበለውን ፡ ተስፋ ፡
እስከ ፡ መስበር ፣ ሊያደርሰው ፣ ክፉኛ ፣ አጉበጠው ። ነገር ፡ ግን ፡
በግፍ ፡ የተመሠረተ ፣ ፍርድ ፡ ከአምላክ ፡ እጅ ፣ የሚመጣው ፡ እውነ
ተኛው ፡ ፍርድ ፡ የሚገለብጠው ፡ መሆኑን ፡ በክርስቲያን ፡ ልቡናችን፡
ስለ ፡ ዐወቅን ፡ የእግዚአብሔርን ፣ የፍርድ ፡ ቀን ፡ በመጠባበቅ ፡ የስ
ደተኝነት ፣ ኑሮዋችንን ፣ በጸሎትና ፡ በማሰብ ፡ ላይ ፡ አስደገፍነው ።

## (ለ) ለስደተኞች ፣ ከግርማዊነታቸው ፣ ቀለብ ፣ ስለመውጣቱ ።

በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩ ፣ ስደተኞች ፣ ዐዋቂና ፣ ልጆች ፡ ቍምር፡
፫፩ ፣ ነበሩ ፣ (ዝርዝራቸውን ፡ በመጨረሻው ፡ ገጽ ፡ ተመልከት ።) ስደ
ተኞቹ ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፣ በኢየሩሳሌም ፡ በየሚስማማቸው ፡ ሰፈር ፡
ቤት ፡ ያዙ ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፣ በገባንበት ፡ የመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ስድ
ስት ፡ ወር ፡ ያህል ፣ ለስደተኛው ፣ ሁሉ ፡ እንደየማዕርጉ ፣ ከግርማዊነ
ታቸው ፡ ቀለብ ፣ እንቀበል ፣ ነበር ።

ከዚያ ፣ በኋላ ፣ የእንግሊዝ ፣ መንግሥት ፣ ወደ ፣ ፓሌስቲን ፡
ሁለት ፣ ሁለት ፣ ሺሕ ፣ ፓውንድ ፣ እየላከ ፣ ሰደተኛው ፣ ከሊቅ ፡
እስከ ፡ ደቂቅ ፣ ሁለት ፡ የፓሌስቲን ፡ ፓውንድ ፡ ተኩል ፡ ከ፶ ፡ ሳን
ቲም ፣ መቀበል ፡ ጀመረ ። ይኸ ፡ ለምግብና ፣ ለልብስ ፡ ሁኖ ፡ ደግሞ ፡
ለብዙዎች ፡ የቤት ፣ ኪራይ ፡ ይከፈል ፡ ነበር ። ስር ፡ ሲድኒይ ፡ ባር
ቶን ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ አቁመው ፡ ለኢትዮጵያ፡
ስደተኞች ፡ ርዳታ ፡ ገንዘብ ፣ ይሰበሰቡ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በቈስ ፡ ማቴ
ዎስ ፡ አማካይነት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፣ ቤት ፡ ይከ
ፈልላቸው ፡ ነበር ። የሆነው ፡ ሁኖ ፡ ከስደተኞቹ ፡ ብዙዎች ፡ በጣም ፡
ተቸግረው ፡ ነበር ። ሁለት ፣ ፓውንድ ፡ ተኩል ፣ ለምግብና ፡ ለል
ብስ ፡ በጣም ፡ ያንስ ፣ ነበር ። ስለ ፡ ሕክምና ፡ ግን ፡ ቈስ ፣ ማቴዎስ ፡
አልፈው ፡ አልፈው ፣ ስለ ፡ ሚረዱ ፣ ጉዳት ፡ አልነበረም ። ፓሌስ
ቲን ፡ በመሐከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ የምትገኝ ፣ አገር ፡ ስለሆነች ፡
በውስጧ ፡ የሚኖሩት ፡ ሕዝቦቿም ፡ የኑሮዋቸው ፡ አካሄድ ፡ ከም
ሥራቅ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ የሚራራቅ ፡ ስላልሆነ ፡ ለእኛ ፡ በኢ
ትዮጵያዊ ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ አላስቸገረንም ፡ ነበር ። በአገሩ ፡ ጤፍ ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ዐውቆ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ለምኖ ፡ መልሱ ፡ አይፈቀድም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ያአሰበውን ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ለመፈጸም ፡ አልተቻለውም ፡ ነበር ።

ከ፲፱፻፳፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ድረስ ፡ የስደተኞች ፡ ማኅበር ፡ ኮሚቴዎች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ስማቸው ፡ የሚታየው ፡ ናቸው ።

የሰዎቹ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ አኳኋን ፡ ተጽፎዋል ።

| | |
|---|---|
| ብፁዕ ፡ እጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | አባል ። |
| ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ | » |
| ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ | » |
| » ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባይነህ ፡ | » |
| » ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ በሀብቴ ፡ | » |
| » ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ | ፕሬዚደንት ፡ |
| » ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ | አባል ፡ |
| » ደጃዝማች ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ | » |
| » ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ | » |
| » ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሩፌ ፡ | » |
| » አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ | ም፡ ፕሬዚደንት ፡ |
| አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኰል ፡ | የሒሳብ ፡ ሹም ፡ |
| በጅሮንድ ፡ አባትሁን ፡ | ግምጃ ፡ ቤት ፡ |
| በጅሮንድ ፡ ረታ ፡ ገብረ ፡ አምላክ ፡ | የሒሳብ ፡ ጸሐፊ ፡ |
| ልጅ ፡ ተድላ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ | የማኅበሩ ፡ ጸሐፊ ፡ |

ከ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ስማቸው ፡ የተዘረዘሩት ፡ በገንዘብ ፡ ያዥነትና ፡ በማኅበሩ ፡ ጸሐፊነት ፡ ተብለው ፡ ገብተዋል ።

| | |
|---|---|
| ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ | ገንዘብ ፡ ቤት ፡ |
| ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ | የማኅበሩ ፡ ጸሐፊ ፡ |

## (ለ) ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ የተስፋ ፡ ማኅበር ።

የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ የተስፋ ፡ ማኅበር ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ማኅበር ፡ የተቋቋመው ፡ ኅዳር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ነው ። ይህ ፡ ማኅበር ፡ የቆመበት ፡ ምክንያቱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥዬ ፡ በምጽፈው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከነበሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቄሶች ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ መግባትና ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ የሰላማዊ ፡ ኢትዮጵያው ያኖች ፡ ገንዘብ ፡ እያታለላቸው ፡ ለኢጣሊያኖች ፡ እጅ ፡ መንሣት ፡ ስለ ፡ ጀመሩ ፡ ነበር ።

የዚህን ፡ የማኅበር ፡ ማቆም ፡ እንደ ፡ ጀመርን ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ «እንግሊዝ ፡ አገር ፡ አስታወቅን ። ግርማዊነታቸውም ፡ "እንደዚህ ፡ «ያለ ፡ ማኅበር ፡ በሌሎቹ ፡ ዘንድም ፡ መቆሙን ፡ ሰምተናል ። ያፈራ «ውን ፡ ግን ፡ ገና ፡ አላየነውምና ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ አሳዩን ፤ በሚ «ቻለው ፡ ሁሉ ፡ እንረዳችኋለን ፤" የሚል ፡ ቃል ፡ ባለበት ፡ አነቃቂ ፡ ደብዳቤያቸው ፡ ፈቀዱልን ። እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ማኅበር ፡ ለማቆም ፡ ከሚኖሩበት ፡ መንግሥት ፡ ማስፈቀድ ፡ የተገባ ፡ ሕጋዊ ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከአዛዥ ፡ ከብደ ፡ ተሰማ ፡ ጋራ ፡ ሁነን ፡ ለጠበቃችን ፡ ለሚስተር ፡ ናታን ማራይን ፡ አማከርን ። ለሚስተር ፡ ማራይንም ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ አሳብ ፡ ገለጽን ፡ የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ የሚ ፈቅድልን ፡ መሆኑን ፡ ስለገለጹልን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ የተስፋ ፡ ማኅበር ፡ የሚቆምበት ፡ አሳብ ፡ በአጭሩ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚዘ ረዘሩት ፡ ዐይነት ፡ መሆኑን ፡ አስረድተን ፡ በሚስተር ፡ ማራይን ፡ ረዳትነት ፡ የፓሌስቲንን ፡ መንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ ለመንን ።

(ሀ) የስደተኞችን ፡ አንድነት ፡ ጠብቆ ፡ ለችግረኞቹ ፡ ኢት ዮጵያውያኖች ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በሚያወ ጣው ፡ ገንዘብ ፡ ለመርዳት ።

(ለ) እያንደ ፡ አንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በወር ፡ አምስት ፡ የፓሌስቲን ፡ ግርሽ ፡ እንዲከፍል ።

(መ) በማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ቢገኝ በት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ የተስፋ ፡ ማኅበር ፡ በወንጀል ፡ ለተከሰሰው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ለጠበቃ ፡ ገን ዘብ ፡ ይከፍላል ። በሚቻለውም ፡ ሁሉ ፡ እንዲረዳ ።

(ሠ) ስለኢትዮጵያዎች ፡ ለሚሆን ፡ ጉዳይ ፡ ማኅበሩ ፡ ፓሌ ስቲን ፡ ፖስት ፡ በሚባለው ፡ ጋዜጣ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አሳቡን ፡ እንዲገልጽ ።

(ረ) ማኅበሩም ፡ በየሳምንት ፡ እሑድ ፡ እየተሰበሰበ ፡ ስለ ፡ ስደተኞች ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመክከር ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

የፓሌስቲንም ፡ መንግሥት ፡ ከዚህ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ የጻፍነውን ፡ አራት ፡ ገጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ይኸ ፡ ማኅበር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ብቻ ፡ እንዲቆም ፡ ፈቀደልን ። ይኸውም ፡ ፈቃድ ፡ ፓሌስታይን ፡ ፖስት ፡ በተባለው ፡ ጋዜጣ ፡ ተጽፎ ፡ ወጣ ።

የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሪዎች ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

| | |
|---|---|
| ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፤ | ፕሬዚደንት |
| » ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ ግዛው ፤ | ጸሓፊ ፤ |
| አቶ ፡ ኪዳኔ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤ | ገንዘብ ፡ ያዥ ፤ |
| » ዱብለ ፡ ሺፈራው ፤ | አባል ፤ |
| » አስፋው ፡ ኤጉታ ፤ | » |
| » ገብሩ ፡ ፃዕሩ ፤ | » |
| » ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ገብሩ ፤ | » |
| አባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፤ | » |
| አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ አማካሪ ፤ | » |

የቀሩት ፡ ማኅበረተኞች ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መጨረሻ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታ ፡ እንዲያደርጉለት ፡ የስደተኞች ፡ ማኅበርን ፡ ጠየቀ ። ፈቃዳቸው ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ርዳታቸውን ፡ በፍጥነት ፡ ሰጡን ። ገንዘቡም ፡ የማኅበሩን ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቤት ፡ ለመከራየት ፡ አስቻለን ። ይህ ፡ ማኅበር ፡ ይሠራው ፡ የነበረውን ፡ በሚቀጥሉት ፡ ገጾች ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጽፌዋለሁና ፡ በዚያው ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።

---

## የኢየሩሳሌም ፡ መነኰሳት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

#### (ሀ) ከኢየሩሳሌም ፡ መነኰሳት ፡ ጥቂቶቹ ፡ ለፋሺስታዊ ፡ ኢጣሊያን ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ መንሣታቸውና ፡ በገዳሙ ፡ ስላነሡት ፡ ሁከት ።

ሠላሳ ፡ አምስት ፡ የሆኑ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ መነኰሳት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ካለው ፡ ከፋሺስታዊ ፡ ኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ ተሰብስበው ፡ ፳ ፡ ፳ ፡ ፓውንድ ፡ ተቀብለው ፡ እጅ ፡ ነሡ ፡ ማለትን ፡ ሰማን ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

መንግሥት ፡ ማወቋን ፡ በመናገርና ፡ መምህሩም ፡ በመንግሥት ፡ የተሾሙ ፡ ስለሆኑ ፡ ከነካህኑ ፡ ለኢጣሊያን ፡ ማስረከብ ፡ የሚቻል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በማስፈራራትና ፡ በሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቍጣ ፡ አስተያየት ፡ እያደረገ ፡ ፋሺስቶች ፡ የተባሉት ፡ ቄሶች ፡ በገዳሙ ፡ ሁነው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የሚያገኙት ፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ እገዛ ፡ አድርጎ ፡ ነገራቸው ።

መምህር ፡ ገሪማም ፡ የቍጣውን ፡ እንፋሎት ፡ እንዳላየና ፡ እንዳልሰማ ፡ ሁነው ፡ በጣም ፡ በቀዘቀዘ ፡ መንፈስ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። «አይቈጡ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ባለው ፡ «እንጂ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ አይፈጸምም ። የኢትዮጵያ ፡ «የፖሊቲካ ፡ አስተዳደርና ፡ የመንፈሳዊ ፡ አስተዳደርዋ ፡ እጅግ ፡ የተ «ለዩ ፡ ናቸው ። አሁን ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ስንነጋገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ «በመንፈሳዊ ፡ አስተዳደርዋ ፡ ማንም ፡ መንግሥት ፡ ለኢጣሊያ ፡ ትገዛ ፡ «የሚል ፡ የለም ። የመንፈሳዊና ፡ የሰላማዊ ፡ አስተዳደር ፡ በእርስዎም ፡ «አገር ፡ በኢጣሊኖችም ፡ አገር ፡ ከሰላማዊ ፡ አስተዳደር ፡ የተለያየ ፡ «ይመስለኛልና ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ «ክርስቲያን ፡ ለኢጣሊያን ፡ እንድትገዛ ፡ ይፈቅዳል ፡ የሚሉት ፡ «አይገባኝም ። እኔም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ አለቆች ፡ እንጂ ፡ «በመንግሥት ፡ አልተሾምኩም ። ገዳሙም ፡ ነጻ ፡ ገዳም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ «ትላንት ፡ እንደተናገርሁት ፡ ሁሉ ፡ እነዚህን ፡ ቄሶች ፡ አልቀበልም ፡ «አሉ ።» ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ከአገረ ፡ ገዢው ፡ ብዙ ፡ «ተከራከርን ።

ሚስተር ፡ ኬትሮች ፡ "ወዲያው ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ ወደኔ ፡ እያየ ፡ "ይኸ ፡ ወጣት ፡ ገና ፡ የመንግሥታትን ፡ ሕግ ፡ ያልተማረ ፡ ነውና ፡ በሱ ፡ ምክር ፡ አይሂዱ ፡ አላቸው» ። እኔም ፡ ለሚስተር ፡ ኬትሮች ፡ "እርግጥ ፡ ነው ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ ነኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በአገር ፡ ጕዳይ ፡ ልጁም ፡ እንደሽማግሌው ፡ መከራከር ፡ አለበት ፡ አልኳቸው» ። ትንሽ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ፡ መምህሩን ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ አዘዙዋቸው ፡ «ስለምግባቸውና ፡ ኑሮዋቸው ፡ ከኢጣሊያን ፡ ቆንስል ፡ ጋራ ፡ እነጋገራለሁ ፡ «እስከ ፡ አዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ ድረስ ፡ ለኢጣሊያን ፡ የገቡት ፡ ቄሶች ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

አትገቡም ፡ በመባባል ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተባሉ ፡ የፋሺስት ፡ መነኰሴ ፡ ሱዳኑን ፡ እነቁት ። ሱዳኑም ፡ አንገታቸውን ፡ አንቆ ፡ አጋደማቸው ፡ የዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከውስጥ ፡ ያሉት ፡ ፋሺስቶች ፡ ለመርዳት ፡ ሲበሩ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የተባሉትን ፡ አቶ ፡ ዱባለ ፡ ሺፈራው ፡ (ተስፋ ፡ ማኅበር ፡ ) አንቆ ፡ በጥፊ ፡ ይወለውላቸው ፡ ጀመረ ፤ የዚያን ፡ ቀን ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩና ፡ እነ ፡ ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ በተቻላቸው ፡ እረዱ ። ከሁሉም ፡ በርታ ፡ ብለው ፡ በከዘራ ፡ ሲጣረጉ የነበሩት ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩና ፡ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ነበሩ ። ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴም ፡ ከዘራቸውን ፡ በጥብቅ ፡ ይዘው ፡ እስከ ፡ ጠቡ ፡ መጨረሻ ፡ ቈይተው ፡ በፖሊሶች ፡ ብዛት ፡ ጠቡ ፡ በርዶ ፡ ከውጭ ፡ መጥተው ፡ የነበሩትን ፡ የፋሺስት ፡ ቄሶች ፡ የቈሰሉትንም ፡ ደኅኖችንም ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ወስደዋቸው ፡ ጠቡም ፡ በረደ ።

( ሠ ) ፋሺስቶች ፡ መነኰሳት ፡ ከደብረ ፡ ገነት ፡ ስለመከልከላቸው ።

መስከረም ፡ ፲፱/፴፩ ዓ. ም. መምህር ፡ ገሪማ ፡ ወደፊት ፡ በሚመጣው ፡ ጠብ ፡ ሁሉ ፡ አላፊው ፡ መንግሥት ፡ እንጂ ፡ እሳቸው ፡ አለመሆናቸውን ፡ ለማመልከት ፡ ወደ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ አብረን ፡ ሄድን ። አገረ ፡ ገዢውም ፡ ምክትል ፡ አገረ ፡ ገዢውን ፡ ማንቴራን ፡ ልኮ ፡ ፖሊስ ፡ ተጨመረ ። የደብረ ፡ ገነት ፡ ፋሺስቶች ፡ ወደ ፡ ዴርሥልጣን ፤ የዴርሥልጣኖችም ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ገነት ፡ እንዳይሄዱ ፡ ተከለከሉ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ጠብ ፡ ሲደረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደርስ ፡ ነበር ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግን ፡ አምስት ፤ ወይም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ደግመህ ፡ በጠብ ፡ ውስጥ ፡ እንዳትገኝ ፤ ከነዚህ ፡ ከተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ በፊት ፡ ተጣልተህ ፡ ብትገኝ ፡ አይቀጡ ፡ ቅጣት ፡ ትቀጣለህ ፡ እያለ ፡ አጥፊውን ፡ ይለቀዋል ። እኛም ፡ እየማቅን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበውን ፡ ስደተኛ ፡ እስኪተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በጠቡ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ እንመክረዋለን ። ጠብ ፡ ከመጣ ፡ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ያደርሰኛል ፡ በማለት ፡ ይታገሣል ። !

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ የዚህም ፡ ገንዘብ ፡ አወጣጥ ፡ (ትርፉን ፡ ነው ፡) ክሬዲ ፡ ሊዮ
ኔም ፡ እንዲያምን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መምህር ፡ የሆነ ፡ የፈረመ
በትና ፡ ማኅተሙም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ማኅተም ፡ መሆኑን ፡
ኢየሩሳሌም ፡ በሚሾሙት ፡ በግሪክና ፡ በካቶሊክ ፡ በሶርያ ፡
ጳጳሳት ፡ ምስክርነት ፡ እንዲሆን ።
፫ ፡ ከእነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ ጳጳሳት ፡ አንደኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠላት ፡
ቢሆን ፡ በሁለቱ ፡ ምስክርነት ፡ ከሦስቱም ፡ ጠላት ፡ ቢሆኑ ፡
የገዳሙ ፡ መምህር ፡ አለቃ ፡ ሰብስቦ ፡ መነኰሳቱ ፡ በአንድነት ፡
በፈረሙት ፡ ምስክርነት ፤
፬ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ግን ፡ በጠላት ፡
እጅ ፡ ቢገባ ፡ በጠላት ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ በዱር ፡ በገደል ፡
ለተሰደዱ ፡ መነኰሳት ፤
፭ ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ የሚሰደዱ ፡ መነኰሳት ፡ ሳይኖሩ ፡ አገሪቱን ፡
በያዘው ፡ ጠላት ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ አገራቸውን ፡ ለቀው ፡
ለሚሰደዱ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፤
፮ ፡ አገራቸውን ፡ ለቀው ፡ ያልተሰደዱ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ባይ
ኖሩ ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ ላሉ ፡ ነዳያኖች ፡ ይሰጥ ።
የዚህም ፡ የውል ፡ ኰፒ ፡ አንድ ፡ በክሬዲ ፡ ሊዮኔ ፡ ባንክ ፤
አንድ ፡ በግሪክና ፡ በካቶሊክ ፡ በሶርያ ፡ ጳጳሳት ፡ እጅ ፤ አንድ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፤ አንድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ እጅ ፡
ይገኛል ፡ ብሎ ፡ ይጨርሳል ።

አሁን ፡ እንግዲህ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለ ፡ ትልቁ ፡ የኢትዮጵያዊ ፡
ቤት ፡ የተደረገውን ፡ ክርክር ፡ እጽፋለሁ ። ቀጥዬ ፡ በክሬዲ ፡ ሊዮኔ ፡
ባንክ ፡ ስለ ፡ አለው ፡ $ 200.000 ብር ፡ የሆነውን ፡ አስረዳለሁ ።

## (ለ) በትልቁ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ቤት ፡ ምክንያት ፡ የተደረገ ፡ ክርክር ።

ይህ ፡ ቤት ፡ ባለፈው ፡ ገጽ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ የመጀመሪያው ፡
ታሪኩ ፡ በግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ የተሠራ ፡ ቤት ፡
ነው ። ይኸ ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ ታዘው ፡ የነበሩት ፡ አቶ ፡ ጳውሎስ ፡
መናምኖ ፡ የተባሉት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቆንስል ፡ የነበሩት ፡
ናቸው ። ቤቱ ፡ ተሠርቶ ፡ እንዳለቀ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ለአቶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

« ነውና ፡ ይኸን ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ ወኪሎች ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ ለቀው ፡
« እጅ ፡ ያዛውሩ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣቸው ፡ ብሎ ፡ አመለከተ ።

የእኛም ፡ ጠበቃ ፡ ናታን ፡ ማራይን ፡ የጊዜ ፡ ማስረዘም ፡ መል
« ሱን ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንንና ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ። ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡
„ ለስደተኞች ፡ መርጃ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ የኪራዩን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ "
" ሰጡ ፡ ለጊዜው ፡ ለማከራየትና ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ እንጂ ፡ "
" ቤት ፡ ለማስረከብ ፡ ውክልና ፡ የላቸውምና ፡ የዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ "
" ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ በእነሱ ፡ "
ላይ ፡ አይደለም ፡ ሲል ፡ መለሰ ። ከብዙ ፡ ክርክር ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡
ይኹ ፡ ክስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ በይና ፡
አቦካሪምስ ፡ ቤይን ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ አዞት ፡ በቀጠሮ ፡
ተለያየን ።

የቀጠሮው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡
ለሚስተር ፡ ማራይን ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ጠበቃቸው ፡ እንዲሆን ፡
እንዲፈቅዱ ፡ የውክልና ፡ ቃል ፡ ተጽፎ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡
ተላከ ። ግርማዊነታቸውም ፡ ሚስተር ፡ ናታን ፡ ማራይን ፡ ባለሙሉ ፡
ሥልጣን ፡ ወኪላቸው ፡ እንዲሆን ፡ ፈቅደው ፡ የውክልናው ፡ ወረ
ቀት ፡ ተላከ ።

### ስለሁለተኛው ፡ ሙግት ።

ኅዳር ፡ ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ ለሁለተኛው ፡ ክርክር ፡ ቀረ
ብን ፡ አቦካሪምስ ፡ ክሱን ፡ እንደ ፡ መጀመሪያው ፡ ቀን ፡ አድርጎ ፡
አቀረበ ።

« ማራይንም ፡ ምንም ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡
ለኢጣሊያ ፡ ተገዢነት ፡ ቢያውቅ ፡ በእንግሊዝ ፡ ተጠባባቂነት ፡ ሥር ፡
ያለችው ፡ የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ አላወቀችምና ፡ ይኸ ፡ ቤት ፡
ለኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ ሊዛወር ፡ አይገባም ፡ » ሲል ፡ የቀን ፡
ማስረዘሚያ ፡ መልሱን ፡ ሰጠ ። ከብዙ ፡ ክርክር ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡
« የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ ለኢጣሊያ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ አላ
ወቀችም ፡ ስትል ፡ በምን ፡ ትደግፋለህ ፡ „ ብሎ ፡ ማራይንን ፡ ጠየ
ቀው ፡ ማራይንም ፡ « በጋዜጣና ፡ በዐዋጅ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ የተነ

www.ethiopianorthodox.org

ገረ ፡ የለም ፡ የፓሌስቲን ፡ ሕዝብም ፡ ይኸን ፡ አያውቅም ፡ » ብሎ ፡ መለሰ ።

አቦካሪዎስ ፡ ቤይ ፡ ከፓሌስቲን ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ ማወቁን ፡ የሚያስረዳ ፡ አንድ ፡ የደብዳቤ ፡ ግልባጭ ፡ አምጥቶ ፡ ኑሮ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አሳይቶ ፡ ተነበበ ።

ማራይን ፡ ግን ፡ ዋናውን ፡ ደብዳቤ ፡ ካላየሁና ፡ አገረ ፡ ገዢ ውንም ፡ ራሱን ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦልኝ ፡ ካልጠየቅሁት ፡ የደብ ዳቤ ፡ ግልባጭ ፡ አልቀበልም ፡ አለ ። ዳኛውም ፡ ከመፍረድ ፡ በፊት ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ዋናውን ፡ ደብዳቤ ፡ ይዞ ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲጠየቅ ፡ አዘዘና ፡ በቀጠሮ ፡ ተለያየን ። አባ ኀ/ር ፡ ከበደና ፡ እኔም ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ጠበቃችንን ፡ እያመሰገንን ፡ ተመለስን ። የየቀኑን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁኔታ ፡ ለመኳንንቶች ፡ እናሰማ ፡ ነበርና ፡ ይኸን ንም ፡ አስታወቅናቸው ።

ይልቁንም ፡ ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ የዓለምን ፡ ፖሊቲካ ፡ በመከ ታተል ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ጋዜጣ ፡ የሚያስነብቡና ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ንም ፡ ሁኔታ ፡ ከጊዜው ፡ የፖሊቲካ ፡ አካሄድ ፡ እያስተያዩ ፡ የሚ ጠባበቁ ፡ ስለነበሩ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ እስትንመለስ ፡ ድረስ ፡ አብ ዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በበረንዳ ፡ ይጠብቁን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የግድ ፡ ማስታ ወቅ ፡ ነበረብኝ ።

የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ ማወቁ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነበር ፡ አገረ ፡ ገዢውም ፡ ዋናውን ፡ ወረቀት ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ እንደሚመ ሰክርብን ፡ የታወቀ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የቀን ፡ ማስረዘሙ ፡ ሐሳብ ፡ ባጭሩ ፡ መቅረቱ ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ብልሃት ፡ መፍጠር ፡ የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ አስገደደን ።

አባ ኀ/ር ፡ ከበደና ፡ እኔም ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ከጠበቃው ፡ ጋራ ፡ ለመመካከር ፡ ሄድን ። ጠበቃውም ፡ አስቦት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ነገረንና ፡ ዋናው ፡ ብልሃት ፡ ገዳሙ ፡ ይኸን ፡ ቤት ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ለእኛ ፡ ብለው ፡ ያሠሩት ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መን ግሥት ፡ ያለፈቃዳችን ፡ በስሙ ፡ አዛውሮት ፡ ቈየ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ አቤቱታችንን ፡ ሳናቋርጥ ፡ ፋሺስታዊው ፡ ጠላት ፡ በድንገት ፡ አገራ ችንን ፡ በመውረሩ ፡ ነገሩ ፡ ሳይፈጸም ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ። አሁንም ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ፡ ቤት ፡ በእኛ ፡ ስም ፡ እንዲዛወርልን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ይታዘዝልን ፡ በሚል ፡ አኳኋን ፡ እንዲከስን ፡ ተማከርን ። ይህም ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተሰማን ። ይኸንን ፡ ከጠበቃችን ፡ ጋራ ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፡ እዛኸ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ለመኳንንቶቹ ፡ አማከሯቸው ። አሳቡም ፡ መልካም ፡ በመሆኑ ፡ መኳንንቶቹ ፡ ከተስማሙበት ፡ በኋላ ፡ የገዳሙ ፡ ማኅበር ፡ እንዲመክርበት ፡ ለመምህሩ ፡ ተነገረ ። የገዳሙም ፡ ማኅበር ፡ ከመከረ ፡ በኋላ ፡ ለመክሰሻው ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ቸገረው ፡ ለመኳንንቶቹ ፡ አስታወቀ ። ከእነሱም ፡ ብዙዎቹ ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታ ፡ ለገዳሙ ፡ ሰጡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቤቱ ፡ የሚድንበትን ፡ መንገድ ፡ ብመፈለግ ፡ ገዳሙ ፡ ዲቪድ ፡ ጉይተን ፡ የተባለውን ፡ እስራኤላዊ ፡ ጠበቃ ፡ ወልዶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ አቀረበ ። እንደዚሁም ፡ ወይዘሮ ፡ አማረች ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ሰባት ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ ኪራዩን ፡ እንድብላ ፡ የሰጡኝን ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ የመንግሥት ፡ ቤት ፡ አድርጎ ፡ ሊወስደው ፡ የማይገባ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ከሰሱ ።

---

የገዳሙና ፡ የኢጣልያኖች ፡ሙግት ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደጻፍኩት ፡ ሁሉ ፡ ገዳሙ ፡ ከሷችኋልና ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ እንድትቀርቡ ፡ የሚል ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደብዳቤ ፡ ለሚስተር ፡ ማራይን ፡ ደረሰው ። ከገዳሙ ፡ ክስ ፡ በፊት ፡ የመጀመሪያው ፡ የኢጣሊያኖች ፡ ክስ ፡ የቀጠሮ ፡ ቀን ፡ ደርሶ ፡ ነበርና ፡ ለዚያ ፡ ቀረብን ፤ በዚሁ ፡ ቀን ፡ የኢጣሊያኖቹ ፡ ጠበቃ ፡ «አቦካሪዎስ ፡ ቤይ ፡» የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ በኢጣሊያን ፡ መገዛት ፡ ማወቁ ፡ ከተረጋገጠ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ንብረት ፡ የሆነው ፡ ቤት ፡ ለኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ ይዛወር ፡» ሲል ፡ አመለከተ ። ሚስተር ፡ ማራይንም ፡ ምንም ፡ የፓሌስቲን ፡ መንግሥት ፡ ዐወቅሁ ፡ ቢል ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ቤቱን ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ለእኛ ፡ ሠርተዋልና ፡ አስረክቡን ፡ ሲል ፡ ከሶን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ለዚሁ ፡ መልስ ፡ እንድንሰጥ ፡ ስለ ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ማራይን ፡ እኔም ፡ የነገሩን ፡ ማስረዘሚያ ፡ ብልሃት ፡ የምንላቸውን ፡ ለማሰናዳት ፡ ከገዳሙ ፡ ጠበቃ ፡ ከዴቪድ ፡ ጉይተን ፡ ጋራ ፡ መሥራት ፡ ጀመርን ። ማንኛውንም ፡ ማስረጃና ፡ ምስክር ፡ ሁሉ ፡ ለገዳሙ ፡ ጠበቃ ፡ አስረከብን ። የእኛም ፡ ጠበቃ ፡ ለገዳሙ ፡ ጠበቃ ፡ አማካሪና ፡ ረዳት ፡ ሆነ ።

---

የቤቱ ፡ ኪራይ ፡ እንዲያዝ ፡ ስለመደረጉ ።

## ክፍል ፡ ፳ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአልኩት ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ የቀጠሮዋችንን ፡ ቀን ፡ ስንጠባበቅ ፡ የኢጣሊያኖቹ ፡ ጠበቃ ፡ የጊዜ ፡ ማስረዘሚያ ፡ ሙግት ፡ መጀመራችንን ፡ ስለ ፡ ተረዳው ፡ የዚህ ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ ገንዘብ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ችግራችንን ፡ እንዳይረዳን ፡ ለማድረግ ፡ ኪራዩ ፡ እንዲያዝልኝ ፡ ብሎ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቤቱታ ፡ ስላቀረበ ፡ እንደገና ፡ ተከሰን ፡ ቀረብን ።

ሚስተር ፡ ማራይንም ፡ «ሕግ ፡ በከለከለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ባልሆነ ፡ በመርዝ ፡ ማርከፍከፍ ፡ የተዋጋችውን ፡ አረመኔ ፡ የኢጣሊያን ፡ ተገዥ ፡ ለመሆን ፡ አንፈልግም ፡ ብለው ፡ የተሰደዱ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ የሚረዱበትና ፡ ለገዳሙና ፡ ለወይዘሮ ፡ አማረችም ፡ የሚሰጥ ፡ ገንዘብ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ አኳኋን ፡ በረጅሙ ፡ ተከራከረ ፡» ለገዳሙና ፡ ለወይዘሮ ፡ አማረች ፡ የሚሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ከኪራዩ ፡ እየተቀነሰ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሆኖ ፡ የቀረው ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ እስከ ፡ ክርክሩ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሾማቸው ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ እጅ ፡ እባንክ ፡ እንዲቀመጥ ፡ » ተብሎ ፡ ተፈረደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡ ከሁለታችሁም ፡ ወገን ፡ ወኪል ፡ የሚሆን ፡ ምረጡ ፡ አለ ፤ አቦካሪዎስም ፡ የእኛም ፡ ጠበቃ ፡ በየወገናቸው ፡ ለቤቱ ፡ ኪራይ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ መርጠው ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንንና ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ቤቱን ፡ ለተሾሙት ፡ ወኪሎች ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ታዘው ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ነገሩ ፡ በመልክም ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቀን ፡ ለዳኝነትና ፡ ለጠበቃም ፡ የምንከፍለው ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ስክርነት ፡ ተጠርቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አቦካሪዎስ ፡ ቤይ ፡ ለርስቱ ፡ ማዘዋወር ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከፍሎ ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ የመዝገብ ፡ ክፍሉም ፡ ሹም ፡ ርስቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ስም ፡ ተፍቶ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንዲዛወር ፡ ማዘዙን ፡ መሰከረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡ የኢጣሊያኖችን ፡ ጠበቃ ፡ አቦካሪዎስ ፡ ቤይን ፡ በብርቱ ፡ ወቅሶ ፡ የርስቱ ፡ ሙግት ፡ እስቲያልቅ ፡ ድረስ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ የከፈሉት ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ እንዲቈይና ፡ ርስቱም ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ እንዲዘገይ ፡ ፈርዶልን ፡ ተመለስን ።

እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ሙግታችን ፡ ልመለስ ። ገዳሙ ፡ እኛን ፡ ከሶ ፡ እንዲሞግተን ፡ በተፈረደው ፡ መሠረት ፡ ቀኑ ፡ ቀጠሮው ፡ ደርሶ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረብን ፡ የገዳሙም ፡ ጠበቃ ፡ ሚስተር ፡ ዴቤድ ፡ ጐይተን ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ይኸን ፡ ቤት ፡ ለገዳሙ ፡ ሲሉ ፡ የሠሩት ፡ ነውና ፡ ልቀቁልን ፡ ብሎ ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለማስረጃ ፡ አቅርቦ ፡ ክሱን ፡ ጀመረ ፡ ሚስተር ፡ ሞሬይን ፡ በመንግሥት ፡ ስም ፡ ሁኖ ፡ "እንዲህ ፡ ያለው ፡ ማስረጃ ፡ ካለ ፡ የምክራክርበት ፡ የለኝም ፡ ሲል ፡ መለሰ ።"

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሙግቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ በኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በኢጣሊያን ፡ መንግሥትና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ባለችው ፡ በኢትዮጵያዊት ፡ ገዳም ፡ መሓል ፡ ሆነ ። ከዚህ ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ የእኛ ፡ ሥራ ፡ ገዳሙ ፡ የሚረታበትን ፡ መንገድ ፡ እየፈለግን ፡ ሥራችንን ፡ ከገዳሙ ፡ መምህርና ፡ ከመጋቢው ፡ ከአባ ፡ ይኄይስ ፡ ጋራ ፡ አደረግን ።

---

የገዳሙና ፡ የኢጣሊያኖች ፡ ሙግት ፡ በይነት ፡
በተለይም ፡ በሁለት ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ ስለማረፉ ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

የገዳሙና ፡ የኢጣሊያኖች ፡ ሙግት ፡ በመንግሥትና ፡ በመንግሥት ፡ መሓል ፡ ከመሆን ፡ መለወጡን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአጭሩ ፡ አስረድቻለሁ ። ስለዚህ ፡ የኢጣሊያኖቹ ፡ ገዳሙን ፡ አከሳሰስ ፡ እንደሚከተለው ፡ ቀረበ ።

www.ethiopianorthodox.org

፩ ፤ መምህሩና ፡ አማኒ ፡ መነኩሳቶችን ።
፪ ፤ የምስሩ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የገዙቱበትን ፡ መጽሐፍ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ምስክሮች ፡ ሁሉ ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ በደንበኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስመስከር ፡ እንዲያመጣ ፡ የ፮ ፡ ወር ፡ ቀጠሮ ፡ ተሰጥቶ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያሉት ፡ ምስክሮች ፡ ቀርበው ፡ እንዲመሰክሩ ፡ ተበየነ ፤ ስለዚህ ፡ ወይዘሮ ፡ አማረችና ፡ ወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ በግል ፡ ገንዘባቸው ፡ ቦታውን ፡ ገዝተው ፡ ቤቱን ፡ መሥራታቸውን ፡ እናውቃለን ፡ ሲሉ ፡ በእኔ ፡ አስተርጓሚነት ፡ ለእኛ ፡ መሰከሩ ።

ስለ ፡ ገዳሙ ፡ ነጻነት ፡ መምህሩ ፡ ተጠይቀው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገዳሙን ፡ በመንግሥት ፡ ሥር ፡ ያለመሆን ፡ ማኅበሩ ፡ ያወጣውን ፡ ሕግና ፡ ሌሎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃ ፡ አስረዱ ።

ለኢጣሊያን ፡ የገቡት ፡ ፋሺስት ፡ ቄሶች ፡ ግን ፡ ገዳሙ ፡ በመንግሥት ፡ አስተዳዳሪነት ፡ የቆመ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ለመመስከር ፡ በኢጣሊያኖቹ ፡ ጠበቃ ፡ ተቈጠሩ ። ከእነሱው ፡ አንደኛው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሚካኤል ፡ የተባሉት ፡ ገዳሙ ፡ ነጻ ፡ ሳይሆን ፡ ተተዳዳሪነቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሥር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ መመስከር ፡ እንደ ፡ ጀመሩ ፡ ነገሩ ፡ በቀጠሮ ፡ ቆመ ።

---

እጼ ፡ ምኒልክ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ አስቀምጠውት ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ $200. 000 (ብር ።)

ክፍል ፡ ፲፩ ።

እረዘም ፡ ያለውን ፡ ክርክር ፡ ለማስረዳት ፡ ስል ፡ ተወት ፡ አድርጌው ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ $ 200.000 ሺ ፡ ብር ፡ ጥቂት ፡ ልጻፍ ።

ባለፉት ፡ ገጾች ፡ እንደ ፡ ጻፍኩት ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ መምህር ፡ እንደ ፡ ተስማሙት ፡ ውል ፡ እያደረጉ ፡ የግሪክንና ፡ የካቶሊክን ፡ የሶርያንም ፡ ጳጳሳት ፡ እያስፈረሙ ፡ በ.3% ትርፍ ፡ ማለት ፡ ( $ 6000 ሺ ፡ ብር ፡ ) በየዓመቱ ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ይቀበሉ ፡ ነበር ። እኛም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረስንበት ፡ ዘመን ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ተቀበሉ ። በነሐሴ ፡ በ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ ግን ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ክሬዲ ፣ ሊዮኔ ፣ ገንዘቡን ፣ የኢጣሊያ ፣ መንግሥት ፣ እንዳስያዘው ፣ ለመክፈል ፡ እንዳልቻለ ፣ ከአሌክሳንድሪ ፣ ወደ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ ገዳም ፣ ጽፎ ፣ አስታወቀ ።

ገዳሙም ፣ ተሰብስቦ ፣ ከመከረ ፣ በኋላ ፣ ባንኩን ፣ ከመክሰስ ፡ በፊት ፣ ወደ ፣ ካቶሊክና ፣ የግሪክ ፣ የሶርያም ፣ ጳጳሳት ፡ እንዲፈርሙላቸው ፣ ሄደው ፣ ጠየቁ ። የካቶሊኩ ፣ ጳጳስ ፣ አልፈርምም ፣ ሲሉ ፣ መልስ ፣ ሰጡ ። የግሪኩ ፣ ጳጳስ ፣ የካቶሊኩ ፣ ጳጳስ ፣ ካልፈረሙ ፣ ለመፈረም ፣ ያዳግተኛል ፣ ሲሉ ፣ እንቢ ፣ አሉ ። የሶርያው ፣ ጳጳስ ፣ ግን ፣ የእኔ ፣ ፊርማ ፣ ብቻውን ፣ ከሠራላችሁ ፣ ምንከፋኝ ፣ አሉ ።

የእሳቸው ፣ ፊርማ ፣ ብቻ ፣ የማይበቃ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ የግርማዊ ፣ አጼ ፣ ምኒልክ ፣ ውል ፡ ወስኖታል ። ስለዚህ ፣ ጠበቃ ፣ ወልዶ ፣ መነጋገር ፣ የሚያስፈልግ ፡ ስለ ፣ ሆነ ፣ ለዚህ ፣ ነገር ፣ እንዲሟገት ፣ ካህናቱ ፣ ሚስተር ፣ ማራይንን ፡ ጠበቃ ፣ ወለዱ ። ሚስተር ፣ ማራይንም ፣ ጳጳሳቱ ፣ ጠላት ፣ የሆኑ ፣ እንደሁ ፣ የመምህሩና ፣ የማኅበሩ ፣ ፊርማ ፣ ገንዘብ ፣ ሊያወጣ ፣ ይችላል ። የሚለውን ፡ የውሉን ፣ ቃል ፣ ጠቅሶ ፣ ቢጽፍ ፣ ባንኩ ፣ በፍርድ ፣ ቤት ፣ ስለታዘዝሁ ፣ በፍርድ ፣ ቤት ፣ እንድሰጥ ፣ ካልተፈቀደ ፣ ልሰጥ ፣ አልችልም ፣ ሲል ፣ መለሰ ።

ሚስተር ፣ ማራይንም ፣ ካይሮ ፣ ድረስ ፣ ሄዶ ፣ በቃልም ፣ ተነጋግሮ ፣ ፍሬ ፣ ሳያገኝ ፣ ተመለሰ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ባንኩ ፣ እንዲከሰስ ፣ ተቈረጠ ። ሚስተር ፣ ማራይን ፣ ካይሮ ፣ አንድ ፣ ወኪል ፣ አድርጎ ፣ ነገሩን ፣ ካስረዳው ፣ በኋላ ፣ በምስር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩ ፣ ተጀመረ ።

---

ከሚያዝያ ፣ ፲፱፻፴፪ ፣ እስከ ፣ ሚያዝያ ፣ ፳፯/፴፫ ዓ. ም.

## ክፍል ፡ ፲፪ ።

ከዚህ ፣ በላይ ፣ የተነገሩት ፣ ከኢጣሊያ ፣ ጋራ ፣ የነበሩን ፣ ክርክሮች ፡ እስከዚህ ፣ ደርሰው ፣ ቆሙ ። አሥጊ ፣ የሆነ ፣ ሦስተኛ ፣ ነገር ፣ ደግሞ ፣ በድንገት ፣ ደረሰ ።

የኢጣሊያኖቹ ፣ ጠበቃ ፣ አዲስ ፡ የተሾሙ ፡ ለገዳሙ ፣ አስተዳዳሪ ፣ ይመጣሉ ፣ ብሎ ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፡ አስታውቆ ፣ የነበረው ፣

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ኑሮ ፡ ጥንት ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሚካኤል ፡ ይባሉ ፡ የነበሩት ፡ አሁን ፡ ኢጣሊያን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘካርያስ ፡ ብሎ ፡ ሰይሟቸው ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ አለቃ ፡ ሊሆኑ ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ. ም በጾመ ፡ አርብዓ ፡ ውስጥ ፡ ኢየሳሩሌም ፡ ደርሰው ፡ ሳን ፡ ጁሊያን ፡ በተባለው ፡ ሆቴል ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ተሰማ ። እኔ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረን ፡ ሁኔታውን ፡ እንድመረምር ፡ ሄድሁ ።

እንዳጋጣሚ ፡ መነኰሴውን ፡ ብቻቸውን ፡ አገኘኋቸው ። ሳያውቁኝም ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ አነጋገርኋቸው ። እሳቸውም ፡ ስለ መሾማቸውና ፡ ስለ ፡ ኢጣልያንም ፡ መንግሥት ፡ ደግነት ፡ በኢትዮጵያም ፡ ከቶ ፡ አርበኛ ፡ የሚባል ፡ እንደ ፡ ሌለና ፡ ጥቂትም ፡ ኑረው ፡ ቢሆን ፡ ኀይለኛው ፡ የቄሣር ፡ ጦር ፡ በታትኖ ፡ ዘሩን ፡ እንዳጠፋው ፡ ከነገሩኝ ፡ በኋላ ፡ ፓስፖርዎን ፡ ያሳዩኝ ፡ ብዬ ፡ ብጠይቃቸው ፡ አሳዩኝ ። ፓስፖራቸው ፡ የሚለው ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ስመው ፡ ለመመለስ ፡ እንጂ ፡ ይኖራሉ ፡ አይልም ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ለኢጣሊያን ፡ የገቡ ፡ ኢትዮጵያዊዎች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ በጉዳትና ፡ በጭንቅ ፡ ይኖራሉ ። ቢሞቱም ፡ አይፈቱ ፤ መቃብራቸውም ፡ እንደ ፡ ማንም ፡ የማጣል ፡ መሆኑንና ፡ ለሀገራቸው ፡ የተሰደዱት ፡ ሁሉ ፡ የሀገሩ ፡ ሰው ፡ ደግፎዋቸው ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ትጋትና ፡ ብርታት ፡ በብዙ ፡ ደስታ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ገዳሙም ፡ ለነጻነታቸው ፡ በሚያስቡት ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ደጃፉን ፡ እንኳ ፡ ለመርገጥ ፡ እንደማይችሉ ፡ ነገርኋቸው ።

እኚህ ፡ ሰው ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ሲነሡ ፡ የተነገራቸው ፡ ገዳሙ ፡ በኢጣሊያኖች ፡ እጅ ፡ ሁኖ ፡ እሳቸውም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ በሹመታቸው ፡ መንበር ፡ የሚቀመጡ ፡ መስሏቸው ፡ ኑሮ ፡ በእኔ ፡ አነጋገር ፡ መደንገጣቸውና ፡ ማዘናቸው ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ ታየኝ ። እንደዚህ ፡ ስንነጋገር ፡ ፋሺስቶቹ ፡ አባ ፡ ወልደ ፡ ሕይወትና ፡ አባ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፤ የካቶሊኩ ፡ መነኰሴ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ መጡ ። እነኚህም ፡ ከሐድያን ፡ መነኰሳት ፡ ያውቁኛልና ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ከዓመት ፡ ይበልጥ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥተውኝ ፡ የማያውቁትን ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥተውኝ ፡ የደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እከ ፡ ምን ፡ አመጣህ ፡ ብለው ፡ ለአዲሱ ፡ ፋሺስታዊ ፡ አለቃቸው ፡ ሊያስተዋውቁኝ ፡ ሞከሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

v

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

(ለ) በትልቁ ፡ የኢትዮጵያዊ ፡ ቤት ።

አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤
ባላምባራስ ፡ አባትሁን ፤
ልጅ ፡ ተድላ ፡ ወንድማገኘሁ ፤ በሕመም ፡ ቤሩት ፡ ሄዶ ፡ ሞተ ።)
አቶ ፡ ከበደ ፡ ጎንደር ፡ ሰው ፡ (በኋላ)
አቶ ፡ ዱባለ ፡ ሺፈራው ፤

(መ) በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ቤት ።

በጅሮንድ ፡ ረታ ፡ ገብረ ፡ እምላክ ፤
ወይዘሮ ፡ የቻለ ፡ መልከም ፤

(ሠ) ሙስራራ ፡ (እልውል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ቤት)

ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፤
ልዕልት ፡ ጽጌ ፡ በሻህ ፤
ወይዘሮ ፡ ብዙነሽ ፡ ካሣ ፤
« ከበደች ፡ ሥዩም ፤
ልጅ ፡ አምኃ ፡ አበራ ፤
« ታሪኩ ፡ አበራ ፤
« ኃይሉ ፡ ካሣ ፤
አቶ ፡ ነቢየ ፡ ልዑል ፤
ግራዝማች ፡ ፀሐይ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፤
ፈለቀች ፡ (የወይዘሮ ፡ ከበደች ፡ አሽከር ፡)

(ረ) ሼህ ፡ ገርራህ ፡ ናህሊት ፡ ኢፀሐቅ ።

ወይዘሮ ፡ ጽጌ ፡ ገብረ ፡ ሩፋኤል ፤
« የምሥራች ፡ እምሩ ፤
« ማርታ ፡ እምሩ ፤
« ጊሩት ፡ እምሩ ፤
« ዮዲት ፡ እምሩ ፤
ልጅ ፡ ሚካኤል ፡ እምሩ ፤
ወይዘሮ ፡ ኤሌኒ ፡ እምሩ ፤
« ዓለም ፡ ሰገድ ፡ ፈቃደ ፡ ምላሴ ፤
« ቱቱ ፡ እምሩ ፤
« ማሚት ፡ እምሩ

www.ethiopianorthodox.org

« ማማሽ ፡ ወርቅ ፡ ሂውጝ ፡
አቶ ፡ ይፍራ ፡ ሸዋ ፡ አሻግሬ ፡
« አሕመድ ፡ አለዊ ፡

ሸ—ሺህ ፡ ኺሩህ ።

ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ።
ወይዘሮ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ጥሩነህ ፡
ወይዘሮ ፡ የወርቅ ፡ ውሃ ፡ አበበ ፡
ሞላ ፡ ንብረቴ ፡ (የወይዘሮ ፡ ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ አሽከር ፡)

ቀ) ሺህ ፡ ኺሩህ ።

አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ቸኰል ፡
ወይዘሮ ፡ መሰለች ።

(በ)—ሺህ ፡ ኺሩህ ።

ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡
ወይዘሮ ፡ ሙሉ ፡ እመቤት ፡ አበበ ፡
« ፍቅርተ ፡ ብሩ ፡
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡
ወይዘሮ ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡ መንገሻ ፡
« እምዩ ፡ አበበ ፡
« አክሊ ፡ ወግ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጉበና ።
ታጠረች ፡
አስቴር ፡ ከበደ ፡ (የታጠረች ፡ ልጅ ፡

(ተ) — ጉልጉታ ።

ጸሓፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሩፊ ፡
በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መንገድ ፡
ቀኛዝማች ፡ ሙሉ ፡ ጌታ ፡ (ኢየሩሳሌም ፡ ሞቱ ፡)

(ቸ) ቤትና ፡ ሰፈር ፡ በመለዋወጥ ፡ የሚኖሩ ።

ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ ግዛው ።
ወይዘሮ ፡ ምሕረት ፡ ጳውሎስ ፡ መናምኖ ፡
አቶ ፡ ከምሱር ፡ ቀረ ፡ ሰራቱ ፡ (ኢየሩሳሌም ፡ ሞተ ፡)

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

አቃ ፡ ገብሩ ፡ ፃዕሩ ፡ (ለኢጣልያኖች ፡ ገብቶ ፡ ፓሴስቲን ፡ የቀረ ፡) ምን ፡ ያስጠንቃል ፡ (የልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ የነበረች ፡ ለኢጣሊያኖች ፡ ገብታ ፡ በኋላም ፡ የተመለሰች ፡) (አሁንም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የቀረች ፡

## ኢያሪኮ ።

ከቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡
ልዕልት ፡ የሸሽወርቅ ፡ ይልማ ።

## የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ የተበሩ ፡ ማኅበር ፡ አባሎችና ፡ ማኅበረተኞች ፡ ስም ።

## ክፍል ፡ ፲፱ ።

### ኰሚቴ ።

ልጅ ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፤ (ፕሬዚደንት ፡)
ልጅ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ግዛው ፤ (ጸሓፊ ፡)
አቶ ፡ ኪዳኔ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤ (ግምጃ ፡ ቤት ፡)
አቶ ፡ ዱባለ ፡ ሺፈራው ፤ (አባል ፡)
አቶ ፡ አስፋው ፡ ኤጐታ ፤ ( ፣ )
አቶ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ገብሩ ፤ ( ፣ )
አቶ ፡ የማነ ፡ ብርሃን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤ ( ፣ )

### ማኅበረተኞች ።

አባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ቀሲስቋሜ ፤
አቶ ፡ ገብሩ ፡ ፃዕሩ ፤ (በኋላ ፡ ለኢጣሊያኖች ፡ ገባ ፡)
አቶ ፡ መሸሻ ፡ ካሣ ፤ (ወደ ፡ ሱዳን ፡ ስንዘምት ፡ ከድቶ ፡ የቀረ ፡)
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ኃይሉ ፤
ልጅ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መድኅን ፤
ልጅ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሣህሉ ፡ ሚካኤል ፤
አቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ዐሸ ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

አቶ ፡ መሐመድ ፡ የሱፍ ። (ወደ ፡ ሱዳን ፡ ስንሄድ ፡ ከድቶ ፡ የቀረ ፡)
አቶ ፡ ይፍሩ ፡ ሸዋ ፡ አሻግሬ ።
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጉበና ።
› ከምሱር ፡ ቀረ ፡ ዅሩቴ ።
ልጅ ፡ አረፈ ፡ ዐይኔ ፡ ሰለባ ።
አቶ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ። (በኋላ ፡ ለኢጣሊያን ፡ ገብቶ ፡ የቀረ ፡)
‹ ገብረ ፡ ኪዳን ።
‹ ነቢየ ፡ ልዑል ።
‹ ወልደ ፡ ሰንበት ፡ ሴርዳ ።
ልጅ ፡ ወርቁ ፡ አድማሴ ።
‹ ከበደ ፡ ማርቆስ ።
‹ ተሰማ ፡ ዘሩ ።
አቶ ፡ ባልቻ ።
አባ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ።
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።
በጅሮንድ ፡ ረታ ፡ ገብረ ፡ አምላክ
አቶ ፡ አሕመድ ፡ አለዊ ።
› አብርሃም ፡ በቂት ።
አባ ፡ አቢየ ፡ እግዚእ ።
አቶ ፡ እንግዳ ፡ መሸሻ ።
› ተገኝ ፡ ቢያድግልኝ ።
› ገብረ ፡ ማርያም ፡ ተድላ ።
› በላይ ፡ ሰጡኝ ።
ግራዝማች ፡ ፀሐይ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ።
ወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ ነሲቡ ።
» አማረች ።
ልጅ ፡ አሰፋ ፡ አበበ ።
አቶ ፡ አፈ ፡ ወረቅ ፡ ኪዳኔ ።
› ያዕቆብ ፡ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ከኢየሩሳሌም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ከድተው ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያን ፡ የገቡ ፡ መነኰሳት ።

## ክፍል ፡ ፰ ።

አባ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፤
አባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፤
አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤
አባ ፡ ተስፋ ፡ ሚካኤል ፤
አባ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፤
አባ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፤
አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤
አባ ፡ ዮሐንስ ፤
አባ ፡ ወልደ ፡ ኪዳን ፤
አባ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፤
አባ ፡ ወልደ ፡ አረጋዊ ፤
ቀሞስ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፤
አባ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፤
አባ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፤
አባ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፤
አባ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
አባ ፡ ተክለ ፡ ሚካኤል ፤
አባ ፡ እንድርያስ ፤
አባ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፤

አባ ፡ ኪዳኔ ፤
አባ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፤
አባ ፡ ዘወልዴ ፤
አባ ፡ አርአያ ፤
አባ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፤
አባ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤
አባ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፤
አባ ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፤
ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ዲያቆን ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ሙሴ ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ኪዳን ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ሚካኤል ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ኪዳን ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ሥላሴ ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ቅዱሳን ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ጊዮርጊስ ፤
እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፤
እማሆይ ፡ አብርሃት ፡ ጽዮን ፤

ቤተ መጻሕፍት

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

